# በሰሜን አሜሪካ የጎንደር ልማትና ኅብረት ድርጅት (ጎልጎድ) መተዳደሪያ ደንብ

## መግቢያ

በሰሜን አሜሪካ የሚኖሩ የጎንደር ክፍለ ሀገር ተወላጆች በግል ኑሮአቸውና በማኅበራዊ ሕይወታቸው በቅርብ እየተገናኙ መተባበርና መረዳዳት አስፈላጊ መሆኑን በመገንዘብ።

የልማት ግብ ሕዝብን ከድህነት ከበሽታ ከመሃይምነት ማላቀቅ ነው። ድህነት ደግሞ የትምሕርትና የጤና ተቋማት አለመኖር ብቻ ሳይሆን የሕዝብ ድምፅ አለመስማት፤ ሀብትና ሥልጣን ማጣት እና ፍትሐዊ አስተዳደር አለመኖር የሚጨምር መሆኑ በዘመናዊ የልማት አስተሳሰብ መሠረት መሆኑን በመረዳት፤

ይህ መተዳደሪያ ደንብ ለሦስተኛ ጊዜ እንዲሻሻል ተደርጎአል።

የጎንደር ልማትና ኅብረት ድርጅት፤ መንግሥታዊ ያልሆነ ለትርፍ የማይሰራና ከማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት የማይወግን ድርጅት ነው።

## ምዕራፍ አንድ

## የድርጅቱ ስምና ዓላማዎቹ

### አንቀጽ 1፥ መጠሪያ ስም

የድርጅቱ መጠሪያ ስም በሰሜን አሜሪካ የጎንደር ልማትና ኅብረት ድርጅት (ጎልጎድ) ይሆናል።

### አንቀጽ 2፥ ዋና ጽ/ቤት

የጎልጎድ ዋና ጽ/ቤት በዋሽንግተን ዲሲ ይሆናል፤ ወይንም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በአጎራባች ስቴቶች በሜሪላንድና በቨርጂኒያ ሊሆን ይችላል።

### አንቀጽ 3፥ ዓላማዎች

የጎንደር ልማትና ኅብረት ድርጅት የተቋቋመዉ ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ ነዉ።

ሀ. ሀገር በቀል የሆነና በራስ የመተማመንን ስሜት ላይ የተመሰረተ የእድገት እንቅስቃሴ አስፈላጊ መሆኑን አባላትና የክፍለ ሀገሩ ሕዝብ እንዲገነዘቡ ማሳወቅ፤ ማስተማር፤ እንዲሁም የጎንደር ክፍለ ሀገር ሕዝብ የኑሮ ሁኔታዉና የምጣኔ ሀብት ደረጃዉ የሚሻሻልበት ሁኔታ እን ዲፈጠር ድርጅቱ ጥረት ያደርጋል።

ለ. የአካባቢዉን ህዝብ ነፃነቱና መብቱ ተጠብቆ ኑሮዉን ለማሻሻል የሚረዱ እቅዶችንና ፕሮግራሞችን ይነድፋል፤ በስራ እንዲዉሉም ያልተቆጠበ ድጋፍ ይሰጣል።

ሐ. በአካባቢዉ የትምህርትና የጤና ተቋማትና አገልግሎት እንዲስፋፉና እንዲሻሻሉ የሚረዱ ቁሳዊና ሌሎች ድጋፎችን ያበረክታል።

መ. ለዘመናት አኩሪ ሆኖ የኖረውን የጎንደር ባህል፤ ታሪክ፤ ስልጣኔ፤ ቅርስ እንዲሁም የተፈጥሮ ሀብቶችን እንዲጠበቅና እንዲዳብር ያደርጋል።

ሠ. በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋ ምክንያት ለሚደርስ ችግር ዕርዳታ ይሰጣል፤ እንዲሁም የወደሙ የልማት ተቋማትን መሻሶ ለማቋቋም በሚደረገው ጥረት ድጋፍ ይሰጣል።

ረ. ድርጅቱ ዓላማዎቹን ለማሳካት ከሚረዱ ብሔራዊና ዓለምአቀፍ ተቋማት ጋር ይተባበራል፤ ድጋፍና እርዳታም ይጠይቃል።

ሰ. በሰሜን አሜሪካ የሚኖሩ የክፍለ ሀገሩን ተወላጆች መተባበርና መረዳዳት እንዲችሉ፣ እን ዲሁም ከላይ የተዘረዘሩትን ዓላማዎች ለማሳካት፤ የድርሻቸዉን እንዲያበረክቱ ለማድረግ ይጥራል።

ሸ. በሰሜን አሜሪካ በተለያዩ ከተሞች የጎልጎድ አባል ድርጅቶች (ቻፕተሮች) እንዲቋቋሙ ጥረት ያደርጋል፤ ድጋፍ ይሰጣል፤ በተጨማሪም በካናዳ፤ በአውሮፓ፤ በመካከለኛው አፍሪካ፤ በአውስትራሊያ፤ በኤዤያና በኒውዝላንድ ተመሳሳይ የትብብርና የልማት ድርጅቶች እንዲቋቋሙ ያነሳሳል፤ ድጋፍ ይሰጣል።

ቀ. ከልማት ጋር በተያያዘ ለሚያጋጥሙ እንቅፋቶችና ችግሮች፤ ክትትልና ጥናት ያካሂዳል፤ እን ደአስፈላጊነቱ በየጊዜው አመች በሆነ መንገድ ለሕዝብ ይፋ ያደርጋል።

## <u>ምዕራፍ ሁለት</u>

## <u>አባልነት</u>

### <u>አንቀጽ 4፥ የአባልነት ዓይነት</u>

ሀ. <u>አባል ድርጅቶች</u> (ቻፕተሮች)
ለ. <u>የእድሜ ልክ አባል</u>፤ በአንድ ጊዜ ሁለት ሺህ ዶላር የከፈለ/ች። በጎልጎድ ጠቅላላ ጉባኤ መሰብሰብና መምረጥ ይችላል/ትችላለች።
ሐ. <u>የክብር አባል</u>፤ ለጎልጎድ ከፍተኛ አገልግሎትና ልዩ የገንዘብ አስተዋጽኦ በማድረግ በድሬክተሮች ቦርድ የተመረጠች በጎልጎድ ጠቅላላ ጉባኤ መሰብሰብና መምረጥ ይችላል።

### <u>አንቀጽ 5፥ የአባልነት መብትና ግዴታ</u>

ሀ. በአንቀጽ ሁለት የተጠቀሱትን ዓላማዎች የሚደግፍና እነዚህን ዓላማዎች ለማስፈፀም በየትኛዉም የሰሜን አሜሪካ ክፍለ ግዛት ወይንም ከተማ የተቋቋመ የጎንደር ልማትና ኅብረት ድርጅት (ቻፕተር) ለአባልነት የተተመነዉን መዋጮ ሲከፍል፥ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (ለ) በተደነገገዉ መሠረት የጎንደር ልማትና ኅብረት ድርጅት አባል መሆን ይችላል።

ለ. አንድ ድርጅት (ቻፕተር) የጎንደር ልማትና ኅብረት ድርጅት መሆን የሚችለዉ፥ ለአባልነት ብቁ መሆኑን የድርጅቱ ቦርድ በድምፅ ብልጫ ሲወስን ነዉ።

ሐ. እያንዳንዱ አባል ድርጅት (ቻፕተር) የጎንደር ልማትና ኅብረት ድርጅት በየሁለት ዓመት በሚያካሂደዉ የአባላት ጠቅላላ ጉባኤ ሁለት አባላቶችን፤ በየአመቱ በሚደረገው የዲሪክተሮች ቦርድ ስብሰባ አንድ ተወካይ ይኖሩታል።

መ. ማንኛዉም አባል በቻፕተር ስብሰባዎች የመሳተፍ፣ ኃሳብ የማቅረብ፣ የመምረጥና የመመረጥ እንዲሁም ጥያቄ የማቅረብና ለጥያቄዉ መልስ የማግኘት መብት አለዉ።

ሠ. አባል ድርጅቶች ከጎልጎድ የተወሰነዉን የአባልነት መዋጮና ሌሎችንም ክፍያዎች በወቅቱ የመክፈል ግዴታ አለባቸዉ።

ረ. አባል ድርጅቶች የጎልጎድ ዓላማዎችና እንቅስቃሴዎች እንዲሳኩ ያልተቆጠበ ጥረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

ሰ. ለሁለት ተከታታይ ዓመት የአባልነት ግዴታ ያላሟላ ድርጅት (ቻፕተር) ከጎልጎድ አባልነት ይሰረዛል።

## <u>ምዕራፍ ሦስት</u>

### <u>አንቀጽ 6፥ ድርጅታዊ መዋቅር</u>

ጎልጎድ የሚከተሉት አደረጃጀት መዋቅር ይኖሩታል።

ሀ. ጠቅላላ ጉባዔ
ለ. ድሬክተሮች ቦርድ
ሐ. ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ
መ. አባል ድርጅቶች (ቻፕተሮች)
ሠ. ጽ/ቤት

## <u>አንቀጽ 7፥ ጠቅላላ ጉባዔ፤ ኃላፊነትና ተግባር</u>

ሀ. ጠቅላላ ጉባኤ የድርጅቱ (ጎልጎድ) የበላይ የሥልጣን አካል ነዉ።

ለ. የድሬክተሮች ቦርድ የሚቀርብለትን የድርጅቱን ፖሊሲ ነክ ጉዳዮች ይመረምራል፥ ያፀድቃል።

ሐ. የድሬክተሮች ቦርድና ኦዲተር ይመርጣል፥ ይሾማል፥ ይሽራል።

መ. የድርጅቱ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ፥ ቦርዱ በሚወስነዉ ቀንና ቦታ በሁለት ዓመት አንድ ጊዜ ይደረጋል። ከአባል ድርጅቶች ቻፕተሮች) 50% ከተገኙ ምልዐተ ጉባዔ ይሆናል።

ሠ. እያንዳንዱ አባል ድርጅት(ቻፕተር) በጠቅላላ ጉባዔ ለመሳተፍና ድምፅ ለመስጠት ብቃት ያላቸዉ ሁለት ተወካዮችን ይመድባል። እንዲሁም ድምፅ የመስጠት መብት ሳይኖራቸዉ በጉባዔዉ ቢሳተፉ፥ የጉባዔዉን አካሄድና ይዘት ያዳብራሉ የሚባሉ ግለሰቦችን በጉባዔዉ እን ዲሳተፉ ለማድረግ ቦርዱ ሙሉ ሥልጣን ይኖረዋል።

ረ. የቦርዱ ሊቀመንበር ወይም የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ወይም ከቦርዱ አባላት መካከል አብዛኛዉን (50%+1) ወገን አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘዉ ጠቅላላ ጉባዔ እንዲጠራ ሊያደርግ ይችላል።

ሰ. የቦርዱ ሊቀመንበር ሳይገኝ/ሳትገኝ፥ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ዲሬክተር፥ የሥራ አስፈጻሚ ዋና ፀሐፊ በጠቅላላ ጉባዔ ሰብሳቢ፣ ም/ሰብሳቢና ዋና ፀሐፊ ሆነዉ ይሰራሉ።

## <u>አንቀጽ 8፥ የድሬክተሮች ቦርድ</u>

ሀ. ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባዔ ሆኖ በሰሜን አሜሪካ የጎንደር ልማትና ኅብረት ድርጅትን በበላይነት የሚመራ የድሬክተሮች ቦርድ ይቋቋማል። የቦርድ አባላት ብዛት በአባል ድርጅቶች (ቻፕተሮች) ተወካዮች ብዛት ይወሰናል። አስራ ሁለት ቻፕተሮች ካሉ የቦርድ አባላት ብዛት ሃያ አራት ይሆናል ማለት ነዉ። ቦርዱ ድርጅቱን ይመራል። ይቆጣጠራል። እንዲሁም የድርጅቱን አጠቃላይ ፖሊሲዎች አዉጥቶ በጠቅላላ ጉባዔ ያፀድቃል።

ለ. የድሬክተሮች ቦርድ ሁለት አይነት አባላት ይኖሩታል። ከቦርዱ አባላት ዉስጥ ግማሹ (50%) የአባል ድርጅቶች ተወካዮች ይሆናሉ። ግማሹ ደግሞ አባል ድርጅቶችን የማይወክሉ አጠቃላይ አባላት ይሆናሉ። እያንዳንዱ አባል ድርጅት በቦርድ ዉስጥ አንድ ተወካይ ይኖረዋል። አጠቃላይ አባላት በጠቅላላዉ ጉባዔ ይመረጣሉ። አጠቃላይ አባላት በሙያቸዉ፤ በልምዳቸዉ፤ ለድርጅቱ ዓላማ መሳካት ባላቸዉ በጎ ፈቃድና ቀናኢነት፤ እንዲሁም ከብሄራዊና ዓለም አቀፍ ዕርዳታ ሰጭ ድርጅቶች ጋር መልካም ግንኙነት ለመፍጠርና ዕርዳታ ለማግኘት ያላቸዉን ብቃትና ዕዉቀና በማመዛዘን ይመረጣሉ።

ሐ. የቦርድ አባላት ቁጥር በአባል ድርጅቶች ብዛት መጠን የሚወሰን ሲሆን እያንዳንዱ አባል ድርጅት በቦርድ ውስጥ በአንድ አባል ይወከላል።

መ. የጎልጎድን መደበኛ ሥራ ለማከናወን አስፈላጊ የሆኑ ወጭዎችን መሸፈን ካልሆነ በቀር፥ የቦርድ አባላት በደመወዝም ሆነ በሌላ መልክ ምንም አይነት ክፍያ አይሰጣቸዉም።

**ሠ.** የቦርድ አባላት የሥራ ዘመን ሁለት ዓመት ይሆናል። ሆኖም የቦርድ አባላት ለተከታታይ የሥራ ዘመን መመረጥ ይችላሉ። አንድ የቦርድ አባል የወከለዉን ድርጅት (ቻፕተር) ሲለቅቅ፥ ወይም ድርጅቱ ዉክልናዉን ሲያነሳ፥ ወይም ያለቦረዱ ፈቃድ ለሦስት ጊዜ በቦርድ ስብሰባዎች ሳይገኝ ሲቀር፥ ወይም በሌሎች ምክንያቶች ኃላፊነቱን መወጣት ሳይችል ሲቀር፥ ቦርዱ በድምፅ ብልጫ ከአባልነት መሰረዝ ይችላል።

**ረ.** የድሬክተሮች ቦርድ፤ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በሚወስነው ቀንና ቦታ በዓመት አንድ ጊዜ ይሰበሰባል። ከቦርድ አባላት ዉስጥ ግማሹ (50%) ሲገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል። ምልዓተ ጉባዔ ከተሟላ፥ ቦርዱ ማንኛዉንም የድርጅቱን ተግባር ማከናወን ወይም ዉሳኔ ማስተላለፍ ይችላል።

**ሰ.** የቦርድ ሊቀመንበር ወይንም የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ወይንም ከቦርድ አባላት 50% + 1 ከጠየቁ አስቸኳይ ወይንም ልዩ የድሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል።

**ሸ.** የቦርድ ስብሰባዎች ከመጠራታቸዉ በፊት የቦርድ አባላት ቢያንስ የአንድ ሳምንት የጽሁፍ ማስታወቂያ ማግኘት ይኖርባቸዋል።

**ቀ.** የጎልጎድ ድሬክተሮች ቦርድ ጠቅላላ ጉባዔዉንና ቦርዱን በሰብሳቢነት የሚመራ አንድ ሊቀመን በር ለሁለት ዓመት የሥራ ዘመን ይመርጣል። አንድ ሊቀመንበር ለሦስት ተከታታይ የሥራ ዘመን ሊመረጥ ይችላል። ለአራተኛ ተከታታይ ዓመት ሊመረጥ አይችልም። ሆኖም አንድ የምርጫ ዘመን ካለፈ በኃላ እንደገና ሊመረጥ ይችላል። የቦርዱ ሊቀመንበር የጎልጎድ ተጠሪ በመሆን ከሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ድሬክተር ጋር በመነጋገርና በመተባበር የሚከተሉት የኃላፊነት ተግባር ይኖሩታል።

1. ከኢትዮጵያ፥ ከኢትዮጵያ ዉጭ ከሚገኙ ድርጅቶችና ግለሰቦች ጋር ግንኙነት በመፍጠር የጎልጎድን ዓላማና ተግባር ያራምዳል።

2. ጎልጎድን በመወከል ብሔራዊና ዓለም አቀፍ ስብሰባዎች ይገኛል፥ ስምምነቶች ይደራደራል፥ ለቦርድ አቅርቦ ሲያፀድቅ ይፈርማል።

3. ለጎልጎድ የሚሰጥ ዕርዳታና ድጋፍ በድርጅቱ ሥም ይረከባል።

4. የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ኃላፊነትና ተግባሩን መወጣቱን ይከታተላል፥ ሪፖርት ለቦርዱ ያቀርባል።

## አንቀጽ 9፥ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ

**ሀ.** ተጠሪነቱ ለድሬክተሮች ቦርድ ሆኖ የድርጅቱን የቀን ተቀን ሥራ የሚከታተልና የሚያስፈጽም 5 አባላት ያሉት የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሲሆን፥ ኮሚቴዉ የሚከተሉት አባላት ይገኙበታል።

1. ድሬክተር
2. ም/ድሬክተር
3. ዋና ጸሐፊ
4. ገንዘብ ያዥ
5. ሂሳብ ሹም

**ለ.** የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የሚመራዉ በድሬክተሮች ቦርዱ ነዉ። የሥራ ዘመኑ ሁለት ዓመት ነዉ። የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ለሦስት ተከታታይ የሥራ ዘመን ሊመረጡ ይችላሉ። ለአርተኛ ጊዜ ሊመረጡ አይችሉም። ሆኖም ከአንድ የሥራ ዘመን ምርጫ በኃላ እንደገና ሊመረጡ ይችላሉ።

**ሐ.** የጎልጎድን መደበኛ ሥራ ለማከናወን አስፈላጊ የሆነ ወጭዎችን መሸፈን ካልሆነ በቀር፥ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በደመወዝም ሆነ በሌላ መልክ ምንም አይነት ክፍያ አይሰጣቸዉም።

አስፈላጊ የሆኑ ወጭዎች አይነትና ተመን በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ተጠንቶ ይወሰናል። የዉሳኔዉ ቃለ ጉባዔ በሰነድነት ይቀመጣል።

## አንቀጽ 10፥ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሹማምንት ኃላፊነትና ተግባር

### ሀ. የሥራ አስፈጻሚ ድሬክተር

1. የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሰብሳቢና ሌሎች የጎልጎድ ጉዳይ ስብሰባዎች በሊቀመን በርነት ይመራል፥ የጠቅላላ ጉባዔና የቦርድ ም/ሊቀመንበር ሆኖ ይሠራል።

2. የጎልጎድን የሥራ እንቅስቃሴዎች በበላይነት ይመራል፥ ይቆጣጠራል። የተቋቋሙ አባል ድርጅቶች (ቻፕተሮች) ተጠናክረዉ የጎልጎድን ዓላማ እግቡ እንዲደርስ አመራር ይሰጣል፥ የሥራ እንቅስቃሴያቸዉን ይከታተላል፥ ይቆጣጠራል፥ የአመራር ድጋፍ ይሰጣል። አዲስ ቻፕተሮች እንዲቋቋሙ ጥረት ያደርጋል።

3. ጎልጎድን በሚመለከት ወጭ ደብዳቤዎች በቦርድ ሊቀመንበር፣ በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ድሬክተር ወይንም ድሬክተሩ በሚወክለዉ ብቻ ይፈረማሉ። የክፍያ ቼክ በድሬክተሩ፤ በዋና ጸሐፊው እና በገንዘብ ያዡ፤ ከሶስቱ በሁለቱ ጣምራ ፊርማ ይሆናል። ማንኛውም ወጭ ክፍያ የሚፈጸመው በቼክ ነው።

4. የጎልጎድን ዓላማ ተግባራዊ ለማድረግ አስፈላጊ ለሆኑ የሥራ እንቅስቃሴዎች የአጭርና የረጅም እቅድ እንዲሁም የዓመት ባጀት አዘጋጅቶ ለቦርድ አቅርቦ ያስወስናል።

5. ኢትዮጵያ ከሚገኙት ከአዲስ አበባ፤ በጎንደርና ደብረታቦር ከተማዎች ከሚገኙ የጎንደር ልማት ማኅበር ጽ/ቤቶችና መሪዎች ጋር እየተገናኘ ለጎልጎድ ዓላማ መሳካት ክትትል ያደርጋል።

6. ከቦርድ ሊቀመንበር ጋር በመነጋገር በኢትዮጵያና ከኢትዮጵያ ዉጭ ከሚገኙ ድርጅቶችና ግለሰቦች ጋር ግንኙነት በመፍጠር የጎልጎድን ዓላማና ተግባር ያራምዳል፥ ጎልጎድን በመወከል ብሔራዊና ዓለም አቀፍ ስብሰባዎች ይገኛል፥ ስምምነቶች ይደራደራል፥ ለቦርድ ቀርቦ ሲፀድቅ ይፈርማል፥ ለጎልጎድ የሚሰጥ ዕርዳታና ድጋፍ በድርጅቱ ሥም ይቀበላል።

7. ለጎልጎድ ዓላማና ተግባር ለማስፈጸም የሚረዱ ልዩ ልዩ ኮሚቴ በማቋቋም አባላት መርጦ በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አቅርቦ ያስወስናል፤

8. ከቦርድ ሊቀመንበር ጋር በመነጋገር የጠቅላላ ጉባዔና የቦርድ ስብሰባ አጀንዳ ያዘጋጃል፥ የስብሰባ ጥሪም ያስተላልፋል።

### ለ. ም/ድሬክተር

1. ድሬክተሩ በማይገኝበት ጊዜ የድሬክተሩን ኃላፊነትና ተግባር ያከናዉናል።

2. ድሬክተሩ የሚመድብለትን ኃላፊነትና ተግባር ያከናዉናል።

### ሐ. ዋና ፀሐፊ

1. የጎልጎድ ጽ/ቤት ተጠሪ ሆኖ የጎልጎድን ማኅተምና ሰነድ ይጠብቃል።

2. የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ፥ የድሬክተሮች ቦርድና የጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባዎች ቃለ ጉባዔ ይመዘግባል ይጠብቃል።

3. ጎልጎድን በሚመለከት የሚዘጋጁ ደብዳቤዎች፤ ሰነዶች ይጽፋል ያዘጋጃል።

4. የክፍያ ቼክ ከድሬክተሩ ወይንም ከገንዘብ ያዡ ጋር ይፈርማል።

**መ. ገንዘብ ያዥ**

1. የጎልጎድን ገንዘብና ንብረት ይይዛል፥ ይጠብቃል።
2. የአባልነት ክፍያዎችንና የዕርዳታ መዋጮዎችን ይቀበላል፥ ደረሰኝ ይሰጣል።

3. የማንኛውም የጎልጎድ ገቢ ገንዘብ በሳምንት ጊዜ ዉስጥ የጎልጎድ ቦርድ በወሰነዉ ባንክ ገቢ መሆን አለበት።

4. ከሥራ አስፈጻሚ ድሬክተር ወይም ከዋና ጸሐፊው ጋር በመሆን በወጭ ቼክ ይፈርማል።

**ሠ. ሂሳብ ሹም**

1. የገንዘብና ንብረት ወጭ ማዘዣ ደብዳቤዎች ይመዘግባል፥ ይይዛል።

2. ወጭና ገቢ መዝገብ ይይዛል። ሪፖርት በየስድስት ወሩ ለሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ፥ በዓመት ለቦርድ ያቀርባል።

## ምዕራፍ አራት

### አንቀጽ 11፥ ልዩ ልዩ ኮሚቴዎች

ሀ. የጎልጎድን ዓላማ ተግባራዊ ለማድረግ የሚረዱ ተጠሪነታቸዉ ለሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የሆኑ ልዩ ልዩ ኮሚቴዎች ይቋቋማሉ።

1. የጎልጎድ ዓላማ የተግባር እንቅስቃሴዎች በየጊዜዉ በጽሑፍ የሚገለጽበት «ልሳነ ጎንደር» መታተሙ ይቀጥላል። ዋና አዘጋጁን ጨምሮ ሦስት አባላት ያሉት የዝግጅት ኮሚቴ (ኤዲተሪያል ኮሚቴ) ይኖራል።

2. የጎልጎድ ዓላማ የሆነዉ ጥራት ያለዉ ትምህርት ለማስፋፋት እንዲቻል ለተወሰኑ የጎንደር ክፍለ ሀገር ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች የትምህርት ማበረታቻ ድጋፍ (ስኮላርሽፕ) መስጠቱ ተጠናክሮ ይቀጥላል። ለዚህ ተግባር የሚረዳ ሦስት አባላት ያሉት የትምህርት (ስኮላርሽፕ) ኮሚቴ ይቋቋማል።

3. ሌሎች ኮሚቴዎች እንደአስፈላጊነታቸዉ በየጊዜዉ በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሊቋቋሙና አባላት ሊመርጡ ይችላሉ።

### አንቀጽ 12፥ ኦዲተር

የጎልጎድ የሂሳብ አያያዝ አሜሪካ የሂሳብ አያያዝ ባለሙያዎች ኢንስቲትዩት ባወጣዉ መሠረት መፈጸሙን የሚያረጋግጥ አንድ የሂሳብ አያያዝ መርማሪ (ኦዲተር) ይመረጣል። ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባዔ ስለሆነ፥ የሂሳብ ምርመራዉን ዉጤት በየአመቱ ለድሬክተሮች ቦርድ፥ በየሁለት ዓመቱ ለጠቅላላ ጉባዔ ያቀርባል።

### አንቀጽ 13፥ መተዳደሪያ ደንብ ማፅደቅ፥ ማሻሻል

1. ይህ መተዳደሪያ ደንብ በጠቅላላ ጉባዔ ከፀደቀበት ጀምሮ የፀና ይሆናል።

2. ጠቅላላ ጉባዔ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘዉ ይህን መተዳደሪያ ደንብ በማንኛዉም ጊዜ ማሻሻል ይችላል። መተዳደሪያ ደንቡን ለማሻሻል ወይንም ለመለወጥ፥ ወይንም ለመሰረዝ በጠቅላላ ጉባዔ አባላት ሁለት ሦስተኛ ድጋፍ ማግኘት አለበት።